# 1ኛ ጴጥሮስ ጥናት (16)

## ጥናት አንድ (1ኛ ጴጥሮስ 1:1-5)

**የጥናት ዓላማ:- ደህንነታችን እግዚአብሄር ጀምሮልን እኛ የምንጨርሰው ነገር ሳይሆን ከጅማሬው አንስቶ  እስከ ፍጻሜው ድረስ በእግዚአብሄር ሃይል የሚከናወን መሆኑን ለመማር::**

**የምናሰላስለው ጥቅስ: «...የተዘጋጀው ድነት  እስከሚመጣ ድረስ በእምነት አማካኝነት በእግዚአብሄር ሃይል ተጠብቃችኋል::» 1ኛ ጴጥ 1:5**

1. በዚህ ክፍል ስለ ፀሐፊው ማንነት የምንማረው ነገር ምንድነው? ስለተጻፈላቸው ሰዎችስ ከክፍሉ ምን ነገሮችን  ያለህ?
2. በዚህ ባነበብነው ምንባብ መሰረት ደህንነ ችንን አስመልክቶ ሥላሴዎች  ያንዳንዳቸው ስላላቸው አስተዋጽዖ ምን ይነግረናል?
3. ጸሐፊውን በቁ 3 ላይ ይህንን ያህል  ግዚአብሄርን ለመባረክ ያነሳሳው ዋነኛ ነገር ምንድነው?
4. በሐዋርያው ጴጥሮስ አነጋገር መሰረት በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት በመነሳት ምክንያት ለአማኝ የተገኙት ሁለት ዋነኛ ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
5. በዚህ ክፍል ውስጥ ስለተዘጋጀልን የርስት ዓይነት የሚናግረንን ሶስት ነገሮች ዘርዝር:: ይህንን ርስት ከምድራዊ ርስት የሚለዩትን ወይም የሚመሳሰልበትን ነገሮች በማነጻጸር ተወያዩበት::
6. ቁ 5 «በመጨረሻ ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀው ድነት...» ዛሬ ድነናል ብለን ለምናምንና ለምንናገር ለ ኛ ይህ አባባል ምን ማለቱ ነው?
7. «..በ ግዚአብሄር ሃይል ተጠብቃችኋል::» ከዚህ አባባሉ የምትረዳው ነገር ምንድነው? ይህንን ሃሳብ ከቁ 2 ጋራ አብረህ በማየት ስለ ደህንነ ችን ጅማሬና ፍጻሜ ምን መቋጠሪያ ሃሳብ ላይ መድረስ ይቻላል ትላለህ?
8. ነዚህ ሰዎች በከባድ መከራ ውስጥ  ያለፉ  ንደሆነ ይ  ወቃል:: ሐዋርያው በዚህ ክፍል የሚናገራቸው  ውነቶች ዛሬ ለሚያልፉበት መከራ ምን ያህል መጽናናት ይሆናቸዋል ብለህ ምናለህ?
9. ደህንነትህ በ ግዚአብሄር ሐይል የሚጠበቅ ነገር መሆኑን ልቦናህ ምን ያህል ተቀብሎ  ል? አኗኗርህ ከዚህ  ውነት ጋራ አብሮ መሄድ አለመሄዱን በጥንቃቄ ለማጤን ጊዜ ውሰድ::

# ጥናት ሁለት (1ኛ ጴጥ 1:6-12)

የጥናት ዓላማ፡- ዛሬ ስለ ጌታ ስም የምናልፍባቸው ፈተናዎች ጌታ ሲገለጥ በፊቱ ምስጋናን፣ ክብርንና፣ ውዳሴን ንደሚያስገኙልን በማወቅ በትዕግስት እንድናልፈው ለማበረታታት።

የምናሰላስለው ጥቅስ: «ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ ጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው።» 1ኛ ጴጥ 1:7

1. ስለ መከራቸው ዘመን ርዝመት ሲናገር ጴጥሮስ ምን ይላል? ከምን ተነስቶ ወይም በምን አውቆ ነው መከራው ለጥቂት ጊዜ መሆኑን የሚናገረው? ስለ ፈተናቸው ዓይነትስ ሌላ የሚናገረው ነገር ምንድነው? ቁ 6-7
2. በመከራ ውስጥ የሚያልፉት አማኞች ስላላቸው ደስ ጸሐፊው ንዴት ነው የሚገልጠው? ተፈጥሯዊ ሰው የዚህን ዓይነት ነገር ሲሰማ የሚሰጠው ምላሽ ምን ይሆናል ብለህ ትገም ለህ? ቁ6-9
3. ነዚህ ክርስትያኖች የሚያልፉበት አስከፊ መከራ ስለመጣበት ምክንያት ጸሐፊው ምን ይላል? ክፍሉን ስናነብ መከራን ሁሉ ለማለፍ የሚረዳ ከአዕምሯችን መጥፋት የሌለበት አንድ ሃሳብ ምንድነው?
4. በጴጥሮሰ አነጋገር ወርቅንና ምነ ችንን በምን መነገድ ማነጻጸር ይቻላል? ኢየሱስን ሳያዩት አደረጉ የሚላቸው ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
5. አማኞች ሁላችን በክርስቶስ ደህንነ ችንን ንዳገኘን ናምናለን። ዲያ በዚህ 1ኛ ጴጥ 1:9 ላይ የሚናገረው « የተቀበላችሁ» የሚለው ሃሳብ ምን ማለቱ ነው?
6. በብሉይ ኪዳን የነበሩት ነብያት ደህንነ ችንን በተመለከተ ያደርጉ የነበረው ነገር ምን ነበረ? ቁ10-12
7. በቁ 10-12 ውስጥ ነብያቱ ያደርጉ ስለነበረው ምርምርና የመላዕክቱ የደህንነ ችንን ምስጢር ለመረዳት መመኘት ስለ ደህንነ ችን የሚነግረን ነገር ምንድነው?
8. መከራህንና የጌ ህን መገለጥ ምን ያህል አያይዘህ ያለህ? በመከራህ መሃል ምን ያህል ሰዎች ጴጥሮስ የሚናገረው አይነት ደስ በህይወትህ ያያሉ? ይህ ዓይነቱ ነገር በሥጋ የሚቻል ንዳልሆነ በመረዳት የመንፈስ ቅዱስን ሃይልና መቻል ለምን?

# ጥናት ሶስት (1ኛ ጴጥ 1:13-25)

የጥናት ዓላማ፡- ከማናቸውም ነገሮች ሁሉ ይልቅ አማኝ ተስፋውን ሊያደርግበት የሚገባው ነገር የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥና እርሱ ሲገለጥ በሚያገኘው ነገር ላይ መሆን እንዳበት ለመማር ነው፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ: ‹‹ስለዚህ ልባችሁን አዘጋጁ፤ ራሳችሁንም ግዙ፤ ተስፋችሁን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለእናንተ በሚሰጠው ጸጋ ላይ ሙሉ በሙሉ አድርጉ፡፡›› 1ኛ ጴጥ 1:13

1. ስለዚህ የሚለውን ቃል ተጠቅሞ ሊያያይዝ የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ ምንድነው? ስለዚህ ካለ በኋላ  ንዲያደርጉ ወይም  ንዲሆኑ የሚጠይቃቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው?
2. ለምንድነው ከሁሉ ነገር መርጦ በተስፋ ላይ  ንዲያተኩሩ የሚመክርበት ምክንያት?
3. በቁ 14-16 ውስጥ በምሳሌነት  ንዲከተሉትና  ንዳይከተሉት የሚያሳስባቸውን ሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ተናገር፡፡ ይህ ክፍል የሚጠይቀው ዓይነት ቅድስና በምን መንገድ ነው ሊደረስበት የሚችለው ብለህ  ምናለህ?
4. ስለ  ግዚአብሄር ባህርይ ቁ 17 የሚናገረው ሃሳብ ምንድነው? ይህ ክፍል የሚነግረን ፍርሃት ምን ዓይነት ፍርሃት ነው? አባ  ችን ከሆነስ ለምን መፍራት አለብን?
5. ስለ ቀድሞ ህይወ  ቸው የሚያስ  ውሳቸው ነገር ምንድነው? ከቀድሞ አባቶቻችሁ የወረሳችሁት ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
6. በቁ 18-21 ውስጥ ለአንባቢዎቹ በግልጽ ሊያስተላልፍላቸው የፈለገው ዋነኛና ቁልፍ ሃሳብ ምንድነው ትላለህ?
7. በወንድማማች መሃል መኖር ስላለበት ፍቅር መጽሐፍ ቅዱሳችን በብዙ ሥፍራዎች ላይ ይናገራል፡፡ በቁ 22 የሰፈረው ከሌሎች የሚለይበት በምንድነው? ዳግመኛ መወለዳችን ከዚህ ሃሳብ ጋራ ለምን  ንደተዛመደ ተናገር፡፡
8. ሥጋ ለባሽ ሁሉ  ንደሳር ክብሩም ሁሉ  ንደሜዳ አበባ መሆኑን መረዳት የወንድማማች መዋደድ  ንዲኖር ሊረዳ የሚችለው በምን መንገድ ነው?
9. የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ምን ያህል ተስፋ ይሰጥሃል? ከዚህ ተስፋ ጋራ የሚሻማ ሌላ ተስፋ ካለህ ዘላቂነት ያለው አንዱና ብቸኛው ተስፋ የጌታ መምጣት ስለሆነ ልብህን በዚያ ተስፋ ላይ ብቻ አድርግ፡፡

# ጥናት አራት (1ኛ ጴጥ 2:1-12)

የጥናት ዓላማ፡- የምድር ላይ ኑሯችን የእንግድነትና የመጻተኛነት ስለሆነ ልባችን በዚህ ዓለም በሚታየው ነገር ተይዞ የዘለዓለማዊውን ነገር ችላ እንዳንል ለማበረታታት፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ: ‹‹ወዳጆች ሆይ፤ በዚህ ዓለም እንግዶችና መጻተኞች እንደመሆናችሁ መጠን፤ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት እንድትርቁ እለምናችኋለሁ፡፡›› 1ኛ ጴጥ 2፡11

1. 1ኛ ጴጥ 2፡1-12 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 ላይ አማኞች እንዲያደርጉ የሚጠየቋቸው ነገሮችን ዘርዝር፡፡ እነዚህ ነገሮችን አድርጉ ሲል የሰጣቸው ምክንያትሰ ምንድነው?
2. በቁ 4 ላይ ስለድንጋዩ የሚናገራቸውን አራት ነገሮች ዘርዝር፡፡
3. « ናንተ ደግሞ...» በማለት በቁጥር 5 ላይ የሚናገረው ስለማን ነው? በ5-6 ላይ እናንተ ስለተባሉት ሰዎች የተነገሩትን ሃሳቦች በሙሉ አንድ በአንድ በመዘርዘር ተወያዩባቸው፡፡
4. «ወደዚህ ህያው ድንጋይ የቀረባችሁ.... ለመሆን ትሰራላችሁ፡፡» ቁ4-5 ከዚህ አባባል ግዚአብሄር ንደሚፈልግብን ሆነን ንድንሰራ ካስፈለገ፤ ግንኙነታችንን አስመልክቶ ማድረግ ሰለሚገባን ነገር የሚጠቁመን ሃሳብ ምንድነው?
5. ቁጥር 9-10ን በማንበብ ይህ « ናንተ» በማለት የሚናገረው ነማንን እንደሆነ ተናገር፡፡ ዚሁ ክፍል ውስጥ ስለ ነዚህ ሰዎች ማንነት ለመግለጽ የተጠቀመባቸውን ቢያንስ ስድስት ሃሳቦች ዘርዝር፡፡
6. በዚህ ክፍል መሰረት አማኝ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት መራቅ ያለበት ምክንያት ለምንድነው? ይህ ሥጋዊ ምኞት ምን ምንን ያጠቃልላል?
7. ‹‹እንግዶችና መጻተኞች›› የሚለው ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ ቢቻል ምሳሌን በመስጠት ተነጋገሩባቸው፡፡ አማኝን በዚህ ዓለም እንግዳና መጻተኛ የሚያደርገው ነገር ምንድነው? ለምን የዚህ አይነቱን ኑሮ ለመለማመድ ያስቸግረናል ብለህ ታምናለህ?
8. ኑሮህን እንደ እንግዳና እንደመጻተኛ ትኖራለህ ወይ? ወገኖችህም በዚህ በከበረ እውነት ላይ ተመርኩዘው እንዲመላለሱ አበረታታ፡፡

# ጥናት አምስት (1ኛ ጴጥ 2፡13-25)

የጥናት ዓላማ፡- ባሪያ ለጌታው ንብረቱ ስለሆነ፤ ሰራ ለአሰሪው ደግሞ ደሞዙን ስለሚከፍለው ይገዛሉ፡፡ አማኝ ግን ከዚህ በተለየ መንገድ ለእግዚአብሄርን እንደሚታዘዝ እያሰበና ውስጣዊ አመለካከቱ የተለየ ሆኖ በአክብሮት ሊታዘዝ እንደሚገባ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እናንተ አገልጋዮች ሆይ፤ ለደጎችና ለገሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለክፉዎቹም በፍጹም አክብሮት ታዘዙ፡፡›› 1ኛ ጴጥ 2፡18

1. 1ኛ ጴጥ 2፡13-25 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ13-15 አማኞች የሚታዘዙት ምን እንዲያደርጉ ነው? ይህ ክፍል ስለሚታዘዙበት ምክንያት ሲሰጣቸው ምነ ይላል?
2. ቁ16 አገልጋዮች (ባሪያዎች) እንደሆኑ ይነግራቸውና ቀጥሎ በነጻነት ኑሩ ይላቸዋል፡፡ እነዚህ ሁለት አነጋገሮች ይቃረናሉ ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን?
3. በቁ17 ላይ አማኞች እንዲያደርጓቸው የታዘዟቸው አራት ነገሮች ምን ምንድናቸው? ለሰው ሁሉ ተገቢ አክብሮትን መስጠት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የራስህን መረዳት ተናገር፡፡
4. ቁ16 ላይ አገልጋዮች የሚላቸውና በቁ18 ላይ አገልጋዮች የሚላቸው የተለያዩ ሰዎች ናቸው ወይ? አስረዳ፡፡ ቁ18 ላይ የተጠቀሱትን የሚያዛቸው ምንድነው? ይህ በኛ ህይወት በሥራ ላይ ሊውል እንዴት እንደሚችል በምሳሌ አስረዳ፡፡
5. ቁ13 ‹‹ስለ ጌታ›› እና ቁ19 ‹‹ስለ እግዚአብሄር›› ይላል፡፡ እነዚህን አነጋገሮች በማየት ሰዎቹ የታዘዙትን ነገር እንእንዲያደርጉ የተጠየቁበት ዋነኛ ምክንያት ለምንድነው?
6. የማያምን ባሪያ ለጌታው ወይም ሰራ ለአሰሪው በግዱ ይገዛል አይደለም ወይ? ታዲያ የአማኝን አገዛዝ ከዚህ እንዲለይ የሚያስፈልገው በምንድነው?
7. የጌታን ፈለግ በብዙ መንገድ እንድንከተል መጽሃፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ በቁ21 ላይ አማኞች እንዲከተሉት የተነገራቸው የትኛውን ፈለጉን ነው? በዚሁ ቁጥር ውስጥ ‹‹የተጠራችሁትም ለዚሁ ነው›› የሚለውንም ሃሳብ በመደረብ፤ አማኝ ስለ መከራ ሊኖረው ስለሚገባው አመለካከት ምን ያስተምረናል?
8. ክፉ አለቃ ገጥሞህ ያቃል ወይ? አማኝ ለአለቃው ማንነት ሳይሆን ለአምላኩ ማንነት ሲል መታዘዝ ስላለበት በአክብሮት መታዘዝን ተለማመድ፡፡

# ጥናት ስድስት (1ኛ ጴጥ 3:1-7)

**የጥናት ዓላማ:- በሚስቶች አኗኗር ያላመኑ ባሎች ወደ እምነት ሊመጡ እንደሚችሉና እንዲሁም ደግሞ የባሎች ሚስቶቻቸውን ማክበር ጸሎት እንዳይከለከል እንደሚረዳ ለመማር::**

**የምናሰላስለው ጥቅስ: «ነገር ግን ውበታችሁ በእግዚአብሄር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ ገርና ጭምት መንፈስ ያለበት፤ ምንጊዜም የማይጠፋ የውስጥ ሰውነት ውበት ይሁን» 1ኛ ጴጥ 3:4**

1. «ሚስቶች ሆይ እናንተም እንደዚሁ...» ሲል መንደርደሪያ አድርጎ ሊጠቀምበት የፈለገው ሃሳብ ምን ነበረ?
2. በቁ 1-2 ሐዋርያው ለሚስቶች የሚሰጠው ምክር ምንድነው? ምክሩን ቢከተሉስ ሊፈራ ስለሚችለው ፍሬ ምን ይናገራል?
3. ቁ3-6 የሴቶችን ውበት በተመለከተ ያስፈራቸውን ውነቶች አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር::
4. ውበትን አስመልክቶ ሐዋርያው ከማን ምሳሌነት ንዲማሩ ነው ሴቶችን ሁሉ የሚጠቁማቸው?
5. የአብርሃም ሚስት ሣራ የውበት ምሳሌ ሆና ልትጠቀስ ያስቻላት ዋነኛው ምክንያት ምንድነው? በዚህ ሃሳብ ላይ ሰፋ አድርጋችሁ ተወያዩበት::
6. «ተስፋቸውን በእግዚአብሄር ላይ የጣሉ...» ቁ 5 ተስፋን በእግዚአብሄር ላይ መጣልና ውበት ሊገናኙ የሚችሉት እንዴት ነው?
7. በቁጥር 7 ላይ ለባሎች የተሰጠው ምክር ምንድነው?
8. «ደካሞች» ሲል በዚህ ክፍል ውስጥ ምን ማለቱ ነው?
9. ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲያከብሩ ምክንያት አድርጎ የሰጣቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው?
10. ለእህቶቻችን፤ መልካም ህይወትን ማሳየት ወይስ በቃል ብዛት ለመመለስ መሞከር የትኛው ይቀላል? ለወንድሞች፤ ሚስትህን ማክበርና የጸሎት ህይወትህን አዛምደህ አይተኸው ታውቃለህ ወይ?

# ጥናት ሰባት (1ኛ ጴጥ 3:8-22)

የጥናት ዓላማ:- በእግዚአብሄር መባረካችን ሌሎችን ለመባረክ እንደሆነ እንድንረዳና የመባረክን ህይወት በለት እለት ኑሯችን እንድንለማመድ ለማበረታታት:::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «...ምክንያቱም እናንተ የተጠራችሁት እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች እያደረጋችሁ በረከትን ለመውረስ ነው::» 1ኛ ጴጥ 3:9

1. «በመጨረሻም ሁላችሁ...» 3:8 በዚህ ሥፍራ ሁላችሁ ሲል ለማጠቃለል ያሰበው እነማንን ነው?
2. በቁ 8-9 አማኝ እንዲለማመዳቸው ሐዋርያው የሚያዛቸውን ነገሮች በመዘርዝር በእያንዳንዱ እምንነት ላይ ተወያዩባቸው:: እንዳይለማመዱ የሚመክራቸው ነገሮችስ ምን ምንድናቸው? ክፉ በሚለው ሃሳብ ላይ ደግሞ ምሳሌ በመስጠት ተወያዩ::
3. ይህ ክፍል የአማኝን መጠራት የሚያያይዘው ከምን ጋራ ነው? በጥሪና በኑሮ መሃል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ምን ያስተምረናል? ኤፌ 4:1
4. በቁ 9 ላይ በረከትን ስለመውረስ የሚናገረው ስለየትኛው በረከት ነው?
5. ህይወትን የሚወድና መልካም ቀኖችን ማየት የሚፈልግ ሰው ማድረግ ያለበትን ነገሮች ዘርዝር:: እነዚህ ሰላምን የመፈለግና የመከተል ርምጃዎች በእርግጠኛነት ሰላምን ያስገኛሉ ማለት ነው ወይ? ካልሆነስ ለምን? ሮሜ 12:18
6. «ክርስቶስን ጌታ አድርጋችሁ በልባችሁ ቀድሱት::» ይህ ማለቱ ሰዎች በማያዩት ሁኔታ ህይወታችንን እንኑር ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ ነው?
7. በቁ 15-16 አማኝ ስላሉት ሁለት ነገሮች ይናገራል:: እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?እነዚህን ሁለት ነገሮች በተመለከተ የማያምኑ ሰዎች ያደርጋሉ ብሎ ሐዋርያው ያስፈራቸው ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
8. «የእግዚአብሄር ፈቃድ እንዲህ ከሆነ...» ሲል መከራን በተመለከተ ምን ማለቱ ነው? ይህንን እውነት ለመግለጽ የክርስቶስ ህይወት ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በምን መንገድ ነው?
9. መንፈሳዊ በረከቶች በሙላት በህይወትህ ሲገለጡ ታያለህ ወይ? ካልሆነስ ምክንያቱ ምን ይመስልሃል? በረከትን በሙላት እንዳንለማመድ ከሚያግዱን ነገሮች አንደኛው ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ጋራ የሚኖረን ግንኙነት ስለሆነ ከዚያ አንፃር ህይወትህ ምን እንደሚመስል መርምር::

# ጥናት ስምንት (1ኛ ጴጥ 4:1-11)

የጥናት ዓላማ:- ለአማኝ በምድራዊ ህይወቱ ከሃጥያት ለመራቅና የእግዚአብሄርን ፈቃድ እያደረገ ለመኖር ከፈለገ ከሁሉ ነገር አስቀድሞ አስተሳሰቡን መቀየር እንደሚገባው ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ: «...እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ እንጂ እንደ ሰው ምኞት እንዳትኖሩ እናንተ ደግሞ ያን ሃሳብ እንደ እቃ ጦረ አድርጋችሁ ያዙት» 1ኛ ጴጥ 4:2

1. 1ኛ ጴጥ 4:1-11 በአንደነት ይነበብ። አሁን ባነበብነው ክፍል ውስጥ ክርስትያን የክርስቶስን ምሳሌነት እንዲከተል የታዘዘው ከምን አኳያ ነው? 1ኛ ጴጥ 2:21-24
2. በጥያቄ ቁ 1 በተወያያችሁት መሰረት አማኝ የክርስቶስን ፈለግ መከተሉ በምድራዊ ህይወቱ ላይ የሚያመጣው አንድና ዋነኛ ለውጥ ምንድነው? የለውጡ እውነተኛነት የሚገለጥባቸውን ነገሮች ዘርዝር።
3. በአስተሳሰባችንና (በአዕምሯችን) ሃጥያትን በመተው መሃል ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ ተናገር። ቁ 1ድን ተመልከት።
4. «...ምክንያቱም በስጋው መከራን የሚቀበል ሰው ሃጥያትን ትቷል።» ይህ አባባል መከራ የተቀበለ ክርስትያን ከዚያ በኋላ ሃጥያት የሚባል ነገር አይነካውም ማለት ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለት ነው?
5. ቁ 7 ላይ ሲጀምር «የሁሉ ነገር መጨረሻ ተቃርቧል...» ይህ የነገር መጨረሻ በመባል የተጠቀሰው ነገር ምንድነው?
6. ንጹህ አዕምሮንና ራስን መግዛትን ለጸሎት ከመትጋታችን ጋራ በማያያዝ ሊናገረን የፈለገበት ምክንያት ለምንድነው ትላለህ?
7. «ፍቅር ብዙ ሐጥያትን ይሸፍናልና...» ቁ 8 ሲል ለሰዎች ጥፋታቸውን የሸፋፍናችሁ እለፉ ለማለት ነው ወይ? ካልሆነ ግን ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ።
8. በቁ7-11 ውስጥ የጌታ መምጣት እየቀረበ በሄደ ቁጥር በኛም ህይወት ውስጥ በትጋት ልንለማመዳቸው የሚገቡንን ቢያንስ አራት ነገሮች ተናገር።
9. «እናንተ ደግሞ ያን ሃሳብ እንደ ዕቃ ጦር አድርጋችሁ ያዙት» የሚለውን ትዕዛዝ ለመታዘዝ የነገር ሁሉ መጨረሻ ተቃርቧል የሚለው ሀሳብ ማበረታቻ ሊሆንህ የሚችለው በምን መንገድ እንደሆነ ተናገር። በየዕለቱ ለሃጥያት ለመሞት አዕምሮህ ምን ያህል ተዘጋጅቷል?

# ጥናት ዘጠኝ (1ኛ ጴጥ 4:12-19)

**የጥናት ዓላማ:- አማኝ መከራን በደስታ ማስተናገዱ ወደፊት ስለሚጠብቀው ነገር ብቻ ሳይሆን ዛሬም ክቡሩ የእግዚአብሄር መንፈስ በእርሱ ላይ ስለሚያርፍ ሊሆን እንደሚገባ ለመማር::**

**የምናሰላስለው ጥቅስ: «ስለ ክርስቶስ ስም ብትሰደቡ፤ የክብር መንፈስ የሆነው የእግዚአብሄር መንፈስ በእናንተ ላይ ስለሚያርፍ ብፁአን ናችሁ::» 1ኛ ጴጥ 4:14**

1. 1ኛ ጴጥ 4:12-19 በአንድነት ይነበብ:: በዚህ ክፍል ውስጥ መከራን በተመለከተ አማኝ ሊኖረው ስለሚገባው አመለካከት ምን ይመክረናል?
2. በዘመናችን በክርስትያኖች አካባቢ መከራን በተመለከተ የሚንጸባረቁት አመለካከቶች ምን ይመስላሉ? ያላመኑ ሰዎች ስለመከራ ያላቸው አመለካከትስ ምን ይመስላል? መከራን በተመለከተ አማኝ ካላመነ ሰው የተለየ አመለካከት ሊኖረው የሚገባው ለምንድነው?
3. በመከራ ጊዜ በአማኝ ህይወት ውስጥ ሊከሰት ስለሚችለው ደስታ ይናገራል:: በምንባቡ መሰረት አማኝ መቼ ነው ይህንን ደስታ የሚለማመደው?
4. በግርፋትና በእስራት እዚህ በምንኖርበት አገር ለጊዜው መከራ የለም:: ሌላ ለክርስቶስ መከራን ልንቀበል የምንችልባቸውን መንገዶች ተናገር::
5. በቁ 12 ላይ «እንደ እሳት የሚፈትን» የሚለው አባባል መከራውን በተመለከተ ቢያንስ ከሁለት ያላነሱ እውነቶችን ይጠቁመናል፤ እነዚህን በመዘርዝር ተወያዩባቸው::
6. በመከራ ውስጥ እያለፍክ ባላህበት ወቅት ከወገኖች መሃል አንዱ «...እንግዳ ነገር እንደ ደረሰብህ በመቁጠር አትደነቅ...የክርስቶስ መከራ ተካፋይ በመሆንህ ደስ ይበልህ::» ቢልህ/ሽ የሚሰማህ ስሜት ምን ይሆናል? ለምን?
7. ስለ ክርስቶስ መከራን ስንቀበል የጌታ ከኛ ጋራ መገኘትና ቅርብ መሆኑን የሚያሳስበን ክፍል ታያለህ ወይ? ካየህ የትኛው ነው?
8. ጸሐፊው ክርስትያን መከራን ሊቀበልላቸው አይገባም ብሎ የዘረዘራቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? «...እግዚአብሄርን ያመስግን እንጂ አይፈር::» የሚለውን እውነት በራሱ ህይወት ጴጥሮስ ተለማምዶ የሚያውቅበት የምታስታውሰውን ክፍል ተናገር::
9. ቁ 19 ላይ የምናነበው «...ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ሰጥተው» የሚለው ስለመከራው ዓይነት ምን ይነግረናል?
10. መከራንና ደስታ አብረው ሊሄዱ የሚችሉ ነገሮች መሆናቸውን አስበህ ታውቃለህ? ከዚህ ርዕስ አንጻር በህይወትህ የተለማመድከው ነገር ካለ ለወገኖች አካፍል::

# ጥናት አስር (1ኛ ጴጥ 5:1-14)

የጥናት ዓላማ፡- የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎችም ሆኑ ምዕመናኑ ትህትናን እንደልብስ መልበስ ከሚጠበቁባቸው ባህርያት ቅድሚያ የሚሰጠው እንደሆነ ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ: «ሁላችሁም እርስ በእርሳችሁ በመከባበር ትህትናን ልበሱ» 1ኛ ጴጥ 5:5

1. 1ኛ ጴጥ 5:1-14 ያለውን በአንድነት አንብቡት፡፡ ምክር ሰጪው ስለራሱ ማንነት የተናገራቸውን ነገሮች ዘርዝር፡፡ የመጀመሪያ ምክሩ ምንድነው?
2. ፀሐፊው «...የእግዚአብሄርን መንጋ ጠብቁ» ሲል ምን ማለቱ ነው? ጴጥሮስ ራሱ በዩሐንስ 21:15-17 ላይ ከተቀበለው ትዕዛዝ ጋራ በማነፃጸር ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል አስረዳ፡፡
3. እግዚአብሄር የመንጋው መጠበቅ ብቻ ሳይሆን እንዴት መጠበቅ እንዳለበትም በዚሁ ክፍል መመሪያ ሰጥቷል፡፡ በቁ2-3 ውስጥ ከዚህ አኳያ የተዘረዘሩት ሃሳቦች ምን ምንድናቸው?
4. ለምንድነው ይህ መንጋ ይህንን ያህል ጥንቃቄ ሊደረግለት የሚያስፈልገው? ሽማግሌዎች መንጋ የሚጠብቁ ከሆነ ፓስተሮችስ ስራቸው ምን ይሆናል?
5. ሽማግሌዎች ይህንን ከባድ ሀላፊነት እንዲወጡ ማበረታቻ እንዲሆን ሐዋርያው ጴጥሮስ የሚነግራቸው ምን እውነት ታያለህ? ሽማግሌዎች በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪነታቸው ለማን ነው?
6. በክፍሉ መሰረትና ዕብ 13:17ን በመመልከት፤ መሪዎች አገልግሎቱ ሸክም ሆኖ እንዳይሰማቸው ለማድረግ መንጋው ምን ማድረግ ይጠበቅበታል? ይህ ትዕዛዝ በምን መንገድ ስራቸውን ያቀልላቸዋል ብለህ ታምናለህ?
7. አጠቃላይ የሆነ ምክርን በቁ 5-9 ባለው ክፍል ላይ አስፍሯል፡፡ እነዚህ ምን ምን እንደሆኑ አንድ በአንድ ተናገር፡፡
8. ከሰጣቸው ምክር አንዱና ዋነኛው «ትህትናን ልበሱ» የሚል ነው፡፡ ይህንን ምክር ተቀብለው በተግባር ላይ ቢያውሉ በሽማግሌዎችና በመንጋው መሃል ለሚኖረው ግንኙነት እንዴት ሊጠቅም እንደሚችል አስረዳ፡፡
9. ትህትናን ለመለማመድ የምትቸገርበትን አንድ ሁኔታ ተናገር፡፡ ለትሁታን ፀጋን ለመስጠት እግዚአብሄር ዝግጁ መሆኑን ማወቅህ ምን ያህል ያበረታታሃል?